# ዘ ሜሴጅ ኢትዮጵያ ነን

**the message.**




## ወደ አፍሪካ መስፋፋት

በ2030 እ.ኤ.አ. አዳዲስ አምስት የአፍሪካ ማዕከላትን ለመክፈት ያለንን ርእያችን እናሳውቃለን!

# ዘ ሜሴጅ ትረስት በ1992 እ.ኤ.አ በማንቸስተር፣ ዩኬ፣ በአንዲ ሃውቶርን ተመሠረተ። በ2014 ደግሞ የመጀመሪያውን ዓለም አቀፋዊ ማዕከል በኬፕ ታውን፣ ደቡብ አፍሪካ የመጀመር እድል ነበረኝ።

## ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ እግዚአብሔር ከምንጠይቀው ወይም ከምናስበው በላይ በእውነት ብዙ ነገር አድርጓል (ኤፌሶን 3:20)።

በ2023 እ.ኤ.አ. ሻውን ፕሪቶሪየስ የተባለው ግለሰብ ዘ ሜሴጅ ደቡብ አፍሪካ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆኑ በአገሪቱ ውስጥ ለአገልግሎቱ አዲስ ዘመን ተጀመረ፣ ይህም በጆሃንስበርግ/ጋውቴንግ የሜሴጅ ማዕከል መጀመርን ያካትታል። ከእኛ ጋር አብረውን ለቆሙና የሜሴጅ ደቡብ አፍሪካን ወደ ፍሬያማነት እና ተነሳሽነት ያላቸው የኢየሱስ ተከታዮች ወደ ሆነ ቡድን እንዲያድግ ስላስቻሉን በዚህ በጣም ተበረታተናል።

በ2023 እ.ኤ.አ. የአፍሪካ ልማት ዳይሬክተር ሆንኩ፣ በዚህም አገልግሎታችንን ወደ አፍሪካ ለማስፋፋት የተሰጠንን ኃላፊነት ለመፈጸም እየተጋሁ እገኛለሁ። ርእያችን በ2030 እ.ኤ.አ በአምስት የአፍሪካ ሃገራት ውስጥ ማዕከሎችን ማስጀመር፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በሚኖሩ ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች በኢየሱስ የምሥራች ወንጌል በቃል እና በተግባር ተፅዕኖ ማድረግ ነው።

በ2024 እ.ኤ.አ የመጀመሪያው ማዕከላችን በካምፓላ፣ ኡጋንዳ ማስጀመራችንን በደስታ አሳውቃለሁ። አሁን ደግሞ በአዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቀጥለውን ማዕከላችንን በማደራጀት ላይ እንገኛለን። የአማካሪ ቡድን የተቋቋመ ሲሆን በ2026 እ.ኤ.አ በይፋ ለማስጀመር በትጋት እየሰራን እንገኛለን።

በዚህ አህጉር ላይ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ብሎ እንዲታይ በጸሎት፣ በማበረታታት እና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ከእኛ ጋር አብረው እንድትቆሙ በአክብሮት እንጠይቃለን።

በክርስቶስ ወንድማችሁ፣



ቲም ታከር
የአፍሪካ ልማት ዳይሬክተር፣ ዘ ሜሴጅ ትረስት





ዘ ሜሴጅ ትረስት በዓለም አቀፍ ዙሪያ የሚንቀሳቀስ ተቋም ሲሆን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር በቃል እና በተግባር ለመድረስ በጣም አስቸጋሪ የሆኑ ወጣቶችን እና የማህበረሰብ ክፍሎች በመሰጠት ያካፍላል።

## ርእያችን



### ወጣቶችን ማብቃት

በመላው ኢትዮጵያ፣ ዘ ሜሴጅ፣ የከተማ ጀግኖች ወይም የወንጌል አርበኛ የሆነ ትውልድ በማስነሳት፣ ተገልለው ያሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች በኢየሱስ ተስፋ እና ዓላማ አግኝተው ማየት ይፈልጋል።



ከኢትዮጵያ ህዝብ 70% የሚሆነው ከ 30 ዓመት በታች ነው። ይህም 89 ሚሊዮን ወጣቶች ናቸው!

### 10 ሚሊዮን

ከ1970 እ.ኤ.አ ጀምሮ በአፍሪካ በየዓመቱ 10 ሚሊዮን የሆኑ ሰዎች ክርስቲያን እንደሚሆኑ ያውቃሉን?

### ቤተክርስቲያንን ማስታጠቅ

በቀለ ሻንቆ፣ 'በአፍሪካ በቤተክርስቲያን ውስጥም ሆነ ከቤተክርስቲያን ውጭ፣ 'የምድር ጨው' እና 'የዓለም ብርሃን' ሆነው የሚኖሩ እና የሚመሩ ሰዎች በእጅጉ አሳሳቢ የሆነ እጥረት አለ።፡ ከኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን ክርስቶስ-ተኮር የለውጥ አመራሮች ለማስነሳት እንፈልጋለን።

### የወጣት ወንጀለኝነትን ማስወገድ

'ከሽብርተኝነት ይልቅ የተደራጀ ወንጀል ለአፍሪካ ልማት የበለጠ ስጋት እየሆነ መምጣቱን ተንታኞች ይናገራሉ። አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት ባጋጠማቸው አስቸጋሪ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ምክንያት ብዙ ወጣቶች በወንጀል ቡድኖች ውስጥ እየተሳተፉ ነው' ጆርጅ አካች

### 27%

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሥራ አጥ ናቸው። የወንጀል መበራከት፣ የወንጀል ቡድኖች እና የድህነት መስፋፋት ከፍተኛ ተግዳሮቶች እንደሚኖረው ይጠበቃል። ለአደጋ-ለተጋለጡ ወጣቶች የእኛ የደቀመዝሙር የማድረግ ፕሮግራማችን የዚህ መልስ አካል ነው።

## ተግባራችን

# ፈጠራ የተካለበት ተልዕኮ

እያንዳንዱ ወጣት የኢየሱስን የምሥራች ወንጌል እንዲሰማ እንፈልጋለን።

ዘመናዊ የተልእኮ ቡድኖቻችን የኢየሱስን የምሥራች ወንጌል በሙዚቃ፣ በትምህርት ቤት በሚሰጡ ትምህርቶች እና ወንጌል-ተኮር የሆኑ ኮንሰርቶችን በማዘጋጀት ፈጠራዊ ክህሎት በታከለበት መልኩ ለወጣቶች ያካፍላሉ።

ሁሉም ወጣቶች ወንጌልን በሚረዱት መንገድ የመስማት መብትና እና ደቀመዝሙር ይደረጉ ዘንድ ደግሞ ከቤተክርስቲያን ማህበረሰብ ጋር መገናኘት እንዳለባቸው እናምናለን። ከዚህ ጎን ለጎን፣ ወጣቶች በሚያገኙት መድረኮች ሁሉ ማለትም፣ በትምህርት ቤቶች እና በጎዳናዎች ላይ የራሳቸውን የተስፋ ታሪኮችን ለሌሎች እንዲያካፍሉ የምናበረታታቸው ሲሆን በዚህም በማህበረሰቦቻቸው ውስጥ ለውጥ ቀስቃሽ ሆነው እንዲያገለግሉ ያስችላቸዋል።









# የማህበረሰብ ለውጥ (ትራንስፎርሜሽን)

ሁሉም ሰው የኢየሱስን የምሥራች መስማት ስላለበት፣ ቡድኖቻችን በጣም አስቸጋሪ ወደሆኑ ቦታዎች  ሄደው ያንኑ ያደርጋሉ!

በጣም አስቸጋሪ በሆኑ የከተማ ሰፈሮች ውስጥ የኢየሱስን የምሥራች ወንጌል በቃል እና በተግባር ለረጅም ጊዜ በዛ ቦታ ቆይታ በማድረግ የሚያገለግሉ ቡድኖችን እናንቀሳቅሳለን። በየአካባቢው ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር ደግሞ ለወጣቶች ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ እንዲኖር ለማስቻል ዘ ሜሴጅ ማዕከላትን በማሰናዳት ለወጣቶች የማጠናከሪያ የትምህርት ድጋፍ ይህም የህይወት ክህሎትን ጨምሮ፣ የደቀመዝሙር ማድረግ፣ የትምህርት ድጋፍ እና አዝናኝ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ለወጣቶች ያዘጋጃሉ፡፡

የማህበረሰብ ማዕከሎቹ ወጣቶች በእለት ተእለት ህይወታቸው እምነታቸውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ እና ከቡድናችን ጋር በመሆን ማህበረሰባቸውን እንዲያገለግሉ እድሎችን እንሰጣቸዋለን።

የእኛ የልብ መሻት ወጣቶች አዎንታዊ በሆነ መልኩ አርአያ ወይም ሞዴል ሊሆናቸው የሚችሉትን ሰዎች በማሳየት ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ሕይወት እንዲኖሩ እና በማህበረሰባቸው ውስጥም ለውጥን የሚያመጡ መሪዎች እንዲሆኑ ለማገዝ ነው።

# እስር-ቤቶች እና ድርጅት

በእስር ቤት ውስጥ ታስረው ያሉትን እንረዳለን።

እንዲሁም ሥራ ለመቀጠር እንቅፋቶች ያለባቸውን አካላት ቀጣይ መጓዝ ያለባቸውን እርምጃ እንዲሄዱ ለማስቻል እገዛ እናደርግላቸዋለን።

የእስር ቤቶች እና የድርጅት ሥራችን ወጣቶች ሊገቡበት የሚችሉትን የወንጀል እና የቡድንተኝነት ዑደት ለመስበር ክርስቶስን-ማዕከል ያደረገና ሁለንተናዊ አቀራረብ ባለው መልኩ ይሰራል።

በእስር ቤት ታስረው ላሉቱ የድጋፍ ስርዓትን እከማዘጋጀት፣ ከማህበረሰብ ጋር ዳግም መቀላቀል፣ የሥራ ዕድል በማመቻቸት ለረጅም ጊዜ የሚዘልቅ እንክብካቤ እና ደቀመዝሙር የማድረግ ድጋፍ  አብረን ለምንሰራው ሠው ሁሉ እናደርጋለን።

የማህበራዊ ድርጅታችን የንግድ ተቋማት ለቀድሞ ወንጀለኞች የሥራ ዕድሎችን ያመቻቻል፣ በዚህም ለእራሳቸው እና ለቤተሰቦቻቸው ድጋፍ እያደረጉ በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ ኢየሱስ ሕይወታቸውን እንዴት እንደለወጠው ለሌሎች ያካፍላሉ።

# ማስታጠቅ እና ማሰልጠን

ቀጣዩን ትውልድ ማሳደግ እና ወንጌልን የሚሰብኩትን ወንጌላዊያንን በማስታጠቅ በእነርሱ በኩል ብዙ ሠዎች ወንጌልን እንዲሰሙ እና ለሌሎችም እንዲያካፍሉ ማስቻል የማንነታችን መሠረት ነው፡፡

ቤተክርስቲያንን እና የእያንዳዱ ሠው ህይወቱ በኢየሱስ እንዲለወጥ እንፈልጋለን፣ በመሆኑም ሠዎች ወንጌልን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ለማስቻል እነርሱን ለማስታጠቅ እና ለማብቃት እንጓጓለን።

በአካባቢው ካሉ አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ጋር በመተባበር ለወንጌል ሥርጭት ሠዎችን ለማስታጠቅ የሚረዳ የወንጌል ሥርጭት- ተኮር የሆነ፣ ዓመቱን-ሙሉ የሚሰጥ ፕሮግራም እና አድቫንስ (የላቀ) አነስተኛ ቡድን የምክር አገልግሎት ብለን እንጠራዋለን፡፡

አገልግሎት ወይም ግራብ ኤ ታውል (ፎጣ ያዝ) የሚባለው በአገልጋይነት ላይ የተመሠረተ አመራር ፕሮግራማችንን በመጠቀም መስራት እንፈልጋለን።



‘አፍሪካ የወጣቶች አህጉር ናት። እነርሱን ከጌታችን ከኢየሱስ የምሥራች ጋር ትርጉም ባለው መልኩ ለማሳተፍ፣ ቤተክርስቲያን ፈጠራ የታከለባቸውን ስልቶች እና ሁለንተናዊ አቀራረብ መከተል ያስፈልጋታል። ዘ ሜሴጅ በአህጉሪቱ እና ከዚያም ባሻገር ያሉትን ወሳኝ ፍላጎቶችን ለማሟላት የታጠቀ ነው’

**ዶ/ር በቀለ ሻንቆ** — የዓለም አቀፍ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የካምፓስ ክሩሴድ ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል



‘ዘ ሜሴጅ ትረስት በኢትዮጵያ ማዕከል ለመክፈት በመዘጋጀቱ በጣም ተደስቻለሁ። የእነርሱ ተለዋዋጭ ወንጌልን ማዕከል ያደረገው አገልግሎት ለረጅም ጊዜ በቃልና በተግባር መካከል እውነተኛ እና ቁርጠኛ ሚዛን ለሚፈልጉ የኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ይኖረዋል። እንደ ዘ ሜሴጅ ይህንን የሚያካትት አገልግሎት ብዙ አላውቅም’

**ሬይመንድ ኤል. ቡከንያ** — ብሔራዊ የቡድን መሪ፣ ትሩ ታንጋዞ




‘ዘ ሜሴጅ ትረስት ሥራ ለእኔ በቀጥታ የኢየሱስን ልብ የሚያንፀባርቅ ነው - ሌሎች  እንደ ችግር የሚመለከቷቸው፣ እውቅና ተሰጥታቸው እና ሥራ ተሰርቶባቸው እንደ መፍትሄዎች እና የተስፋ ተሸካሚዎች ተደርገዋል’

**ሱዛና ፋር** — ዋና ሥራ አስፈፃሚ, ጎልደን - ዩዝ ኤንድ ጎልደን - ዩዝ አንተርፕራይዝ



ዘ ሜሴጅ ትረስት ለአደጋ የተጋለጡ ወጣቶች ላይ ያሳደረውን ከፍተኛ ተጽዕኖ በግሌ አይቻለሁ፣ ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ በገንዘብ ራሳቸውን የቻሉ እና ለሌሎች አርአያ የሚሆኑ ወጣቶች እንዲሆኑ ለውጦአቸዋል። ዘ ሜሴጅ ትረስት ፕሮግራሞች በዓለም ዙሪያ በሁሉም ማዕዘናት ተስፋፍቶ ማየት ድንቅ ነገር ነው’

**ካሮሊን ኤ. ኦፒንዴ** — መስራች እና ዋና ሥራ አስፈፃሚ, ዘ ኤንጂኦ ዊስፐር፣ሴንተር ፎር ሶሻል ኢምፓክት



‘ዘ ሜሴጅ ትረስትን መውደድ ብቻ ሳይሆን የከተማ ሚስዮናውያን ወይም የወንጌል አርበኞችን ለማሳደግ የሚያደርጉትን አስደናቂ ሥራም እንዲሁ እወዳለሁ። እነዚህ አካላትን ለመድረስ እጅግ-አስቸጋሪ የሆኑትን ወጣቶችን ለመድረስ ይችላሉ፡፡ እንደ ዘ ሜሴጅ ያሉ ድርጅቶች እያደረጉ ያሉትን ለማድረግ ከዚህ የተሻለ ጊዜ የለም’

**ሉክሶሎ ኬንታኔ** — ብሔራዊ ዳይሬክተር, አልፋ ደቡብ አፍሪካ

# ምስክርነት

# አብረውን ማገልገል ይፈልጋሉ?

ይጸልዩ

ይቀላቀሉ

ይለግሱ

ኢሜይል:- africa@messageglobal.org

messageglobal.org

ዘ ሜሴጅ ኢትዮጵያ

The Message Trust is a registered data user and only uses personal data in connection with its charitable purposes. Registered Office: Lancaster House, Lancaster Campus, Harper Road, Sharston, Manchester, M22 4RG. The Message Trust is a company limited by guarantee, registered in England and Wales No. 3961183 Registered Charity No. 1081467 VAT Registration No. GB 727 177616